ምክንያተ ፡ ጽሒፎቱ ፡ ለሐዋርያ ፡ ኀበ ፡ ቲቶ ።

እስመ ፡ ጳውሎስ ፡ ሰበከ ፡ ቀዳሚ ፡ በሀገረ ፡ ቀርጤስ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወአብኦሙ ፡ ኀበ፡ ሃይማኖት ።

ወእምድኅረ ፡ ንስቲት ፡ መዋዕል ፡ እንዘ፡ የሐውር ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ብሔር ፡ ኀደጎ ፡ ህየ ፡ ለቲቶ ፡ ረድኡ ፡ ከመ ፡ ይገሥጾሙ ፡ ኢያ ምጽኡ ፡ ካልአ፡ ትምህርተ ፡ ወዛውዓ ፡ ነገር ፡ ወመሐድምተ ፡ዕቤራት ፡ ዘይፈጥሩ ።

ወአዘከሮ ፡ ዙሎ ፡ እከያቲሆሙ ፡ ለሰብአ ፡ ቀርጤስ ፡ ዘኮነ ፡ እምኔሆሙ ።

ወአዘዞ ፡ ከመ ፡ ይዛለፎሙ ።
ወዓዲ ፡ አዘዞ ፡ ከመ ፡ ይሢም ፡ ጳጳሳተ ፡ወቀሲሳነ ፡ ለለአህጉር ።

ወአርአዮ ፡ ዘከመ ፡ ይደልዎሙ ።

ወዙሉ ፡ ነገሩ ፡ ወትእዛዙ ፡ ለዝንቱ ፡ መልእክት ፡ ይመስል ፡ ከመ ፡ መልእክተ ፡ ጢሞቴዎስ፡ ቀዳማዊ ።

ወጼሐፈ ፡ ሎቱ ፡ ዘንተ ፡ መልእክተ ፡ እንዘ፡ ሀሎ ፡ ብሔረ ፡ ናቆጵል ።

ወፈነዎ ፡ በእደ ፡ አርጣማ ፡ ረድኡ ።

ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ለቲቶ ፡ ከታብ ፡ የጻፈበት ምክንያት ።

ጳውሎስ ፡ አስቀድሞ ፡ ቀርጤስ ፡ በምትባል፡ ሀገር ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ስም ፡ አስተምሮ ፡ ወደሃይማኖት ፡ መልሷቸው ፡ ነበረ ።

ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ወደሌላ ፡ ሀገር ፡ሲሔድ የባልቴቶችን ፡ ተረት ፡ አሪትን ፡ ወይም ፡ ከልባቸው ፈጥረው ፡ ሌላ ፡ ትምህርት ፡ እንዳያመጡ ፡ ይገሥጻቸው ፡ ዘንድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩን ፡ ቲቶን ፡ ከዚያ፡ ትቶት ፡ ሔዶ ፡ ነበረ ።

የቀርጤስ ፡ ሰዎች ፡ የሚሠሩትን ፡ ክፋታቸውን ፡ ኹሉ ፡ እያስታወሰ ፡ ጻፈለት ፡

በቁርጥ ፡ እንዲዘልፋቸው ፡ አዘዘው ።
ዳግመኛም ፡ ጳጳሳቱንና ፡ ቀሳውስቱን ፡ በየሀገሩ ፡ እንዲሾም ፡ አዘዘው ።

ጳጳሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ ሊያደርጉት ፡ የሚገባቸውንም ፡ ገለጸለት ።

የዚህ ፡ ከታብ ፡ ነገሩም ፡ ትእዛዙም ፡ ኹሉ ፡ የጢሞቴዎስን ፡ የመጀመሪያውን ፡ ከታብ ፡ ይመስላል ።

ይህን ፡ ከታብ ፡ ናቆጵል ፡ በሚባል ፡ ሀገር ፡ ሳለ ፡ ጻፈለት ።

በደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ በአርጣማ ፡ እጅ ፡ ላከለት።

www.ethiopianorthodox.org

ቲቶ ፡ የቀርጤስ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እናቱም ፡ አባቱም ፡ አረማውያን ፡ ናቸው ፡ በኃ ፡ ብላቴናነቱ ፤ አይቶ ፤ ከፍጹምነት ፡ እንዲደርስ ፡ ዐውቆ ፡ አስከትሎታል ፡ ሲያስከትለውም ፡ ሳይገዝር ፡ አስከትሎታል ፡ ወቲቶስ ፡ ዘምስሌየ ፡ እንዘ ፡ አረማዊ ፡ ውእቱ ፡ ኢያገበርከዎ ፡ ይትገዘር ፡ እንዲል ። ኋላም ፡ ከፍጹምነት ፡ እንደደረሰ ፡ ዐውቆ ፡ በቀርጤስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ሹሞታል ፡ ኋላም ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሹም ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አትሹም ፡ እያለ ፡ ሲያጸና ፡ ጽፎ ፡ ይሰድለታል ፡ ምክንያቱ ፡ እንደ ፡ ቀዳማዊ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ነው ። ለመስተካህድ ፡ ብእሲ ፡ እምከመ ፡ ምዕረ ፡ ወካዕበ ፤ ገሠጽኮ ፡ ወእበየ ፡ ኅድጎ ፡ ወእምር ፡ ከመ ፡ ዓላዊ ፡ ውእቱ ፡ ዘከማሁ ፡ ያስሕት ፡ ወያጌጊ ። ወእምከመ ፡ ፈነውኩዎ ፡ ለአርጢሞን ፡ ኀቤከ ፡ አው ፡ ጢኪቆስ ፡ ፍጡነ ፡ ነዓ ፡ ኀቤየ ፡ ሀገረ ፡ ናቆጵል ፡ እስመ ፡ አጥባዕኩ ፡ አክርም ፡ ህየ ፡ ለዜማስ ፡ ጸሐፊ ፡ ሀገር ፡ ወለአጵሎስ ፡ ጽሑቀ ፡ አክብሮሙ ፡ ከመ ፡ ኢይጸንሱ ፡ ምንተኒ ፡ ወአለ ፡ እንኒ ፡ ይትመሀሩ ፡ ትምህርተ ፡ ሠናየ ፡ በዘይቀውሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስተ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ግብር ፡ እምኀ ፡ ኵሎ ፡ ዘያፈቅረኒ ፡ በሃይማኖት ፡ ይላል ፡ የጻፈበት ፡ ሀገር ፡ ናቆጵል ፡ ከታብ ፡ ወሳጅ ፡ አርጣማ ፡ ረድኡ ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፡ እምጳውሎስ ፡ ገብሩ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዩ ፡ ከምኾን ፡ ከኔ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ ከታብ ። ወሐዋርያሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሃይማኖቶሙ ፡ ለኅሩያኒሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።

በአብርሃም ፡ በይስሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንቼ ፡ ብገኝ ፡ ሰውን ፡ አጸና ፡ ዘንድ ።

ወበአእምሮ ፡ ጽድቅ ፡ ዘበጽድቁ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ባንድነት ፡ ጸንቶ ፡ ያለ ፡ ሦስትነትን ፡ በሦስትነት ፡ ጸንቶ ፡ ያለ ፡ አንድነትን ፡ በማመን ፡ ጸንቼ ፡ ብገኝ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሾመኝ ። አንድም ፡ (በሃይማኖቶሙ ፡ ለኅሩያኒሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ) በነቢያት ፡ በሐዋርያት ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንቼ ፡ ብገኝ ።

ወበአእምሮ ፡ ጽድቅ ፡ ዘበጽድቁ ፡ ለእግዚአብሔር ።

በትንቢተ ፡ ነቢያት ፡ ጸንቶ ፡ ያለ ፡ ሥጋዌውንም ፡ በማመን ፡ ጸንቼ ፡ ብገኝ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሾመኝ ፡ ከኔ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ ከታብ ፡ ፡

፪ ፤ ወበተስፋ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ ዘአሰፈወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኢይሔሱ ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ።

(ዘአሰፈወ ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ ) ተናግሮ ፡ የማያስቀር ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ባናገረው ፡ የዘለዓለም ፡ በሚኾን ፡ በሕይወት ፡ አለኝታ ፡ ጸንቼ ፡ ብገኝ ። አንድም ፡ ስውን ፡ አጸና ፡ ዘንድ ፡ ከሾመኝ ።

ወአርአየ ፡ ቃሎ ፡ በዕድሜሁ ፡ በስብከተ ፡ ዚአነ ፡ ኪያሁ ፡ (ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፱ ፡ ፲ ።

እኛ ፡ እሱን ፡ በማስተማራችን ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ አካላዊ ፡ ቃልን ፡ የገለጠ ። አንድም ፡ ወንጌልን ፡ የገለጠ ።

ወተአመነኒ ፡ ሊተ ፡ ላዕሌሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መድኃኒነ ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፩-፲፩ ።

ሑሩ ፡ ወመሀሩ ፡ ባለው ፡ ትእዛዝ ፡ ለሐዋርያነት ፡ ትብቃለህ ፡ ያለኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባናገረው ፡ ተስፋ ፡ ጸንቼ ፡ ብገኝ ። አንድም ፡ ስውን ፡ አጸና ፡ ዘንድ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ክሾመኝ ፡ ከኔ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ ከታብ ።

ለቲቶ ፡ ወልድየ ፡ ዘአፈቅር ፡ በተፋቅሮ ፡ ወበሃይማኖት ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፪ ። )

በሃይማኖት ፡ በፍቅር ፡ ጸንቶ ፡ ምግባር ፡ ሲሠራ ፡ ባገኘው ፡ ለምወደው ፡ ለልጄ ፡ ለቲቶ ፡ ትድረስለት ።

ሰላም ፡ ለከ ። ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ ቸር ፡ እስህን ።

ወጸጋ ። ሐዋርያነት ፡ ይጽናልህ ።

ወሣህል ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኃኒነ ።

ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንድ ፡ ይቅርታ ፡ ይደረግልህ ።

፫ ፡ እስመ ፡ እንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ኀደጉከ ፡ ውስተ ፡ ቀርጤስ ፡ ከመ ፡ ታስተራትዕ ፡ ዘተርፈ ።

ከኔ ፡ የቀረውን ፡ ታከናውን ፡ ዘንድ ፡ ስለዚህ ፡ በቀርጤስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ሹሜሃለሁ ፡ አኮን ። እንድም ፡ በቀርጤስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ሹሜሃለሁና ፡ እንዲህ ፡ የሾምሁህ ፤ ከኔ ፡ የቀረውን ፡ ታከናውን ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

እንድም ፡ አእምር ፡ ይላል ፡ ታከናውን ፡ ዘንድ ፡ እንደኾነ ፡ ዕወቅ ።

ወትሚም ፡ ቀሲሳነ ፡ ለለአህጉር ።

በየሀገሩ ፡ ቀሳውስትን ፡ ትሾም ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ ትሾም ፡ ዘንድ ፡ እንደኾነ ፡ ዕወቅ ፡ (ሐተታ ፡ ) ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ ሳንድ ፡ አውራጃ ፡ አንድ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ሳንድ ፡ አውራጃ ፡ አንድ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ይሾማል ፡ እንደ ፡ ጎጃም ፡ እንደትግሬ ፡ እንደ ፡ ጐንደር ፡ ባለው ። ቄስ ፡ ግን ፡ በየሀገሩ ፡ ካልኾነ ፡ አይኾንምና ፡ ለለአህጉር ፡ አለ ።

በከመ ፡ አዘዝኩከ ።

በቀዳማዊ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ እንደአዘዝሁህ ፡ (ሐተታ ፡ ) ያንዱንስ ፡ ሳንዱ ፡ አያመጣም ፡ ብሎ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ እንዳዘዝሁህ ።

፯ ፡ ብእሴ ፡ ዘእሐተ ፡ ብእሲተ ፡ አውሰበ ።

ያልደጋገመ ፡ ይሾም ።

ኅሩይ ። ደግ ።

ዘኢየሐምይዎ ፡ በእኩይ ።

በከፉ ፡ ነገር ፡ የማያነሡት ።

ዘቦ ፡ ውሉድ ፡ መሃይምናን ።

የተሠሩ ፡ የተቀጡ ፡ ልጆች ፡ ያሉት ፡ ይሾም ።

ዘኢያስተዋድይዎሙ ፡ በምርዓት ።

በድርዓት ፡ የማይከሷቸው ፡ የማያጣሏቸው ።

አለ ፡ ኢኮኑ ፡ ዝሉፋነ ።

ኃጢአት ፡ አዘውታሪዎች ፡ ሴሰኞች ፡ ደፋሮች ፡ ተሳዳቦች ፡ ያልኾኑ ።

አለ ፡ ይትኤዘዙ ። (፩ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፪ ። ፮ ፡ ጺዋ ፡ ፳ ፡ ፫ ።

የተሠሩ ፡ የተቀጡ ።

፰ ፡ ወርቱዐ ፡ ይሠየም ፡ ጳጳስ ፡ ዘአልቦ ፡ ሐሜት ።

ምክንያተ ፡ ኃጢአት ፡ የሌለበት ፡ ቅስና ፡ ሊሾም ፡ ይገባል ።

ዘኢያደሉ ።

በፍርድ ፤ በብያኔ ። በትምህርት ፤ በጸሎት ፤ በምጽዋት ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ የማያደላ ።

ከመ ፡ መጋቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ (፩ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፩ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፳፬ ። )

መጋቢ ፡ እግዚአብሔር ፤ እንደመኾኑ ፡ እንደመጋቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደፀሐይ ፡ እንደሙሴ ፤ እንደ ፡ ጌታ ፤ እንደቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፤ እንደእስጢፋኖስ ፤ እንደራሱ ።

ዘኢኮነ ፡ መዓትመ ።

ቁጡ ፡ ያይደለ ።

ዘልቡብ ።

ገራም ። እንድም ። (ዘልቡብ) ፡ ዐዋቂ ።

ዘኢያበዝኅ ፡ ሰትየ ፡ ወይን ።

አብዝቶ ፡ የማይጠጣ ፡ አይጠጣ ፡ አላለም ።

ወኢያፈጥን ፡ እዴሁ ፡ ለዘቢጥ ።

ፈጥኖ ፡ የማይማታ ፡ ፈጥኖ ፡ የማይገዝት ።

ወዘኢያፈቅር ፡ ንዋየ ፡ ከንቶ ።

ኃላፊውን ፡ ከብት ፡ የማይወድ ።

፱ ፡ መፍቀሬ ፡ ነግድ ።

እንግዳ ፡ ተቀባይ ።

ዘሠናይ ፡ ምግባሩ ።

ግብሩ ፡ ያማረ ፡ የበጀ ።

ዘአንጽሐ ፡ ርእሶ ።

ሰውነቱን ፡ ከኃጢአት ፡ የለየ ።

ጻድቅ ። እውነተኛ ።

ወኄር ። ቸር ።

www.ethiopianorthodox.org

ወየዋሀ ፡ ቅን ።
ወመሥተዓግሥ ።
ትዕግሥት ፡ ያለው ።

፱ ፡ ዘያንሐሲ ።
ነገር ፡ አላፊ ፡ ልበ ፡ ሰፊ ።
ዘምሁር ፡ ቃለ ፡ ሃይማኖት ።
የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ የተማረ ።
ዘይከል ፡ ገሥጾ ፡ በትምህርተ ፡ ሕይወት ። (፪ ተሰ ፡ ፪ ፡ ፲፭) ።
ሕይወት ፡ በሚገኝበት ፡ በወንጌል ፡ ትምህርት ፡ መምከር ፡ ማስተማር ፡ የሚቻለው ።
ወይዘልፎሙ ፡ ለእለ ፡ ይትዋሥኡ ።
የሚከራከሩትንም ፡ የሚረታ ፡ ይኹን ። ተከራክሮ ፡ የማይረታ ፡ አለና ።

፲ ፡ እስመ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ኢይትኤዘዙ ።
ለወንጌል ፡ የማይታዘዙ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ።
ወነገሮሙኒ ፡ ከንቱ ።
ነገራቸው ፡ ከንቱ ፡ አሪት ፡ የሚኾን ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ።
ወያስሕትዎሙ ፡ ለጽሉላነ ፡ ልብ ።
ልበ ፡ ደነቋርት ፡ የኾኑትን ፡ ያስቷቸዋልና ።

፲፩ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለእለ ፡ እምአይሁድ ፡ እለ ፡ ርቱዕ ፡ ይፍጽምዎሙ ፡ አፉሆሙ ። (ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፴፬ ። )
ይልቁንም ፡ ምላሽ ፡ ሊያሰጣቸው ፡ ከሚገባ ፡ ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ የሚኾኑትን ፡ የሚረታ ፡ ሊኾን ፡ ይገባል ።
እስመ ፡ እሉ ፡ ይገፈትዑ ፡ አብያተ ፡ ኵሉ ። (፪ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፮ ፡)
እሊህ ፡ የሰውን ፡ ኹሉ ፡ ልቡና ፡ ይለዋውጣሉና ።
ወይሜህሩ ፡ በዘኢይደሉ ።
በማይገባ ፡ ያስተምራሉና ።
በዘይረብሖሙ ፡ ኀሳር ።
ጥቅማቸው ፡ ኃሳር ፡ በሚኾንባቸው ፡ ገንዘብ ።

፲፪ ፡ ወናሁ ፡ ይቤ ፡ እሑዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ነቢዮሙ ፡ በእንቲአሆሙ ።
የነሱንም ፡ ነገር ፡ ከሳቸው ፡ አንዱ ፡ መምህራቸው ፡ ተናግሯል ።
እስመ ፡ ሰብአ ፡ ቀርጤስ ፡ መደልዋን ፡ ሐሳውያን ፡ ዘልፈ ።
የቀርጤስ ፡ ሰዎችማ ፡ እንጂ ፡ ግብዞች ፡ ዘወትር ፡ ሐሰትን ፡ የሚናገሩ ፡ ናቸው ፡ አኮ ፡ ብሎ ።
አራዊት ፡ እኩያን ፡ ከርሠ ፡ መካን ።
አራዊት ፡ እኩያን ፡ ናቸው ፡ አኮ ፡ (ከርሠ ፡ መካን) ፡ ፅዕድ ፡ ስቁርት ፡ ይላታል ፡ ሰሎሞን ፡ ያች ፡ ውኃ ፡
እንዳትቋጥር ፡ ዘር ፡ የማትቋጥር ፡ ሲል ፡ እሊህንም ፡ ምሥጢር ፡ የማያቋጥሩ ፡ ሲል ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ (ሐተታ
እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወዴት ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ተናግሮት ፡ ሳይጻፍ ፡ የቀረ ፡ ነው ፡ ተናግሮ ፡ ሳይጻፍ ፡ የቀረውንም ፡
ማምጣት ፡ ልማድ ፡ ነው ። አንድም ፡ ወትከውን ፡ ቀርጤስ ፡ ፂአተ ፡ መራዕይ ፡ ያለውን ፡ ሶፎንያስ ፡ እን
ዲህ ፡ ለውጦ ፡ አነበበው ። አንድም ፡ ዜውስ ፡ በግብሩ ፤ ዲዮናስዮስ ፡ በነገሩ ፡ ተናግሮታል ፤ ስዲ ፡ ጳው
ሎስ ፡ ግን ፡ ወደናንት ፡ ያልመጣ ፡ ኢዩጴዴስ ፡ የሚባል ፡ ነቢይ ፡ ተናግሮታል ፡ ብሏል ።

፲፫ ፡ ወዝንቱ ፡ ስምዕ ፡ እሙን ፡ ላዕሌሆሙ ። (፪ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፪ ፮ ። )
ይህ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ የታመነ ፡ ምስክር ፡ ነው ።
በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተዛለፎሙ ፡ ምቱረ ።
ስለዚህ ፡ ቁርጥ ፡ አድርገህ ፡ ተከራከራቸው ።
ከመ ፡ ይጠይቁ ፡ በሃይማኖት ።
ሃይማኖትን ፡ ይረዱ ፡ ዘንድ ።

፲፬ ፡ ወኢያምጽኡ ፡ መኃድምት ።
ተረት ፡ አሪትን ፡ እንዳያመጡ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወሥርዓተ ፡ ስብእ ።
ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ትምህርት ፡ አሪትን ፡ እንዳያስተምሩ ።
ዘይመይጣ ፡ ለጽድቅ ፡ (፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፯ ። )
ወንጌልን ፡ የሚለውጣት ፡ ብሉ ፡ ለአሪት ፡ ቀጠለ ።

፲፭ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘኮነ ፡ ንጹሕ ፡ ለንጹሓን ፡ (ማቴ ፡ ፲፭ ፡ ፲፩ ፡ ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፳ ።
የተፈጠረ ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ለንጹሓን ፡ ንጹሕ ፡ እንጂ ፡ ነው ።
ወለርኩሳንስ ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ አልቦሙ ፡ ንጽሕ ፡ ምንትኒ ።
ድል ፡ ለተነሡ ፡ ላላመኑ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ንጽሕ ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ የላቸውም ።
እስመ ፡ ርኩስ ፡ ሕሊናሆሙ ።
ልቡናቸው ፡ ድል ፡ የተነሣ ፡ ነውና ።

፲፮ ፡ ወበልቦሙ ፡ የአምኑ ፡ ከመ ፡ ዘያእምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።
በልቡናቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደሚያውቁት ፡ አድርገው ፡ እናምናለን ፡ ይላሉ ።
ወይከህድዎ ፡ በምግባሮሙ ።
በሥራቸው ፡ ግን ፡ ይክዱታል ።
ርኩሳን ፡ እሙንቱ ፡ ወከሃድያን ።
ድል ፡ የተነሡ ፡ ከሃድያን ፡ ናቸው ።
ወምኑናን ፡ በውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ (፪ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፰ ። )
በበጎው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ተርታዎች ፡ ናቸው ።

---

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፪ ።

፩ ፡ ወአንተሰ ፡ ንግር ፡ ዘይደሉ ፡ ለትምህርተ ፡ ሕይወት ፡ (፩ጢሞ ፡ ፯ ፡ ፫ ፡ ፪ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።
አንተ ፡ ግን ፡ ተርታ ፡ እንዳትባል ፡ ልታስተምረው ፡ የሚገባህ ፡ ሕይወት ፡ የሚገኝበትን ፡ ትምህርት ፡
ሥራውን ፡ እየሠራህ ፡ አስተምር ።

፪ ፡ ሊቃውንትኒ ፡ ይኩኑ ፡ ንጹሓነ ፡ እምዝሙት ።
ሽማግሎችም ፡ ከዝሙት ፡ ንጹሓን ፡ ይኹኑ ፡ ይኹኑ ፡ ዘንድ ፡ አስተምር ፡ (ሐተታ ፡ ) ከዚህ ፡ እንዲህ ፡
እለ ፡ ሲራከም ፡ ፫ተ ፡ ግብራተ ፡ አስቆረረት ፡ ነፍስየ ፡ እንዘ ፡ አረጋዊ ፡ ዘማዊ ፡ ወእንዘ ፡ ባዕል ፡ ደንጻዊ ፡
ወእንዘ ፡ ነዳይ ፡ ዕቡይ ፡ ብኋል ።

ወንቁሓነ ፡ ከንዋመ ፡ ሐኪት ፡ የነቁ ፡ ይኹኑ ።
ወጠቢባነ ። ዐዋቆች ፡ ይኹኑ ።
ወኢይናፍቁ ፡ በሃይማኖት ።
ሃይማኖትን ፡ አይጠራጠሩ ።
ይትፈቀሩ ፡ ፍቅርን ፡ ይያዙ ።
ወይለብዉ ፡ ያስተውሉ ።
ወይትዓገሡ ፡ ይታገሡ ።

፫ ፡ ልሒቃትሂ ፡ ከማሁ ፡ ይትቀደሳ ።
ባልቴቶችም ፡ ሴቶች ፡ ሊቃውንትኒ ፡ ይኩኑ ፡ ንጹሓነ ፡ እንዳልሁ ፡ ንጹሓን ፡ ይኹኑ ።
ወያሠንያ ፡ ግእዞን ።
ግብራቸውን ፡ ያከናውኑ ።
ኢያስተሐውራ ፡ ነገረ ።
ነገር ፡ እያዋሰዱ ።
ወኢይትቀነያ ፡ ለስቴ ፡
ለመጠጥ ፡ አይገዙ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወኢይስጠያ ፡ ውስተ ፡ ስካር ።

ስክረው ፡ ወድቀው ፡ ተዘርረው ፡ አይደሩ ፡ (ሐተታ ፡ ) ስካር ፡ ሲዘፍኑ ፡ ሲያጨበጭቡ ፡ ማደር ፡ ነው ፡ ስጥየት ፡ ነዊምሰ ፡ ዘይመስል ፡ መዊተ ፡ እንዲል ፡ (ተግ ፡ ዮሐ ፡ አፈ ፡ ) ከነዚያው ፡ እጥቶት ፡ ወድቆ ፡ ተዘርሮ ፡ ማደር ፡ ነው ። ዳዕሙ ፡ ይገሥጻ ፡ ወይምሐራ ፡ ሠናየ ፡ ትምህርተ ፡ ለአንስት ።

በጎውን ፡ ትምህርት ፡ ለሕፃናቱ ፡ ለሴቶች ፡ ያስተምሩ ፡ ይምከሩ ፡ እንጂ ።

ከመ ፡ ያንጽሓ ፡ ርእሶን ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ። )

ሰውነታቸውን ፡ ከኃጢአት ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ።

፬ ፡ ወንኡሳትሂ ፡ ያፍቅራ ፡ አምታቲሆን ፡ ወውሉዶን ።

ሕፃናቱም ፡ ሴቶች ፡ ባሎቻቸውን ፡ ልጆቻቸውን ፡ ይውደዱ ።

ኢይዘምዋ ።

መውደዱም ፡ ይፀ ፡ ነው ፡ ከሌላ ፡ አይሕዱባቸው ።

ወይግበራ ፡ ሠናየ ።

በጎውን ፡ ሥራ ፡ ይሥሩ ።

ወያሠንያ ፡ ግእዞን ፡

ግብራቸውን ፡ ያከናውኑ ፡

ወሥርዓተ ፡ ቤቶን ።

የቤታቸውን ፡ ሥራ ፡ ያከናውኑ ፡ (አለ) ፡ ቤተ ፡ ለቦቻቸውን ፡ ሠርተው ፡ ቀጥተው ፡ ያሳድሩ ።

ወይትአዘዛ ፡ ለአምታቲሆን ፡ (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፪ ። )

ለባሎቻቸው ፡ ይገዙ ።

ከመ ፡ ኢይፅርፍ ፡ አሐዱሂ ፡ ላዕለ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

አንድ ፡ ሰውስ ፡ እንኳ ፡ ወንጌልን ፡ እንዳይነቅፍ ፡ በወንጌል ፡ ማመን ፡ ሴት ፡ ለባሏ ፡ ላትገዛ ፡ ነው ፡ ብሎ ።

፮ ፡ ወለወራዙትኒ ፡ ገሥጾሙ ፡ ያንጽሑ ፡ ርእሶሙ ።

ሕፃናቱም ፡ ወንዶች ፡ ሰውነታቸውን ፡ ከኃጢአት ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፡ ምክራቸው ፡ አስተምራቸው ።

ወይኩኑ ፡ ጠቢባነ ።

ዐዋቆች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ።

፯ ፡ ወኩኖሙ ፡ አርአያ ፡ ወአምሳለ ፡ ለኵሎሙ ፡ በምግባረ ፡ ሠናይ ።

ፀበጎው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አብነት ፡ ኹናቸው ።

ወይኩን ፡ ነገርከ ፡ ወትምህርትከ ፡ በንጽሕ ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፫ ።

የምትናገረው ፡ ነገር ፡ የምታስተምረው ፡ ትምህርት ፡ በንጽሕና ፡ ይኹን ።

፰ ፡ ወበሥሩዕ ፡ ነገር ።

በተከናወነ ፡ ነገር ፡ ይኹን ።

ዘአልቦ ፡ ነውር ።

ነውር ፡ ነቀፋ ፡ የሌለበት ፡ ይኹን ።

ዘኢይሜንኖ ፡ አሐዱሂ ።

አንድ ፡ ሰውስ ፡ እንኳ ፡ ቸል ፡ የማይለው ፡ ይኹን ።

ከመ ፡ ይትኀፈር ፡ ጸላዒ ።

ጸላዒ ፡ ዲያብሎስ ፡ ይገሠጽ ፡ ዘንድ ።

ወይኅጣዕ ፡ ዘይነብብ ፡ ላዕሌነ ፡ ሕሡመ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፭)።

በኛ ፡ ላይ ፡ የሚናገረው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳያገኝ ።

ክፍል ፡ ፪ ።

፱ ፡ ነባሪኒ ፡ ይትአዘዙ ፡ ለአጋእዝቲሆሙ ።

ቤተ ፡ ሰብአችም ፡ ለጌቶቻቸው ፡ ይገዙ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወያሥምርዎሙ ፡ በኵሉ ። (ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፭ ፡ ፩ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፩ ፡ ፩ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ።
በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ያሰኘዋቸው ። ወኢይቅስጡ
ከብት ፡ እያነሣሡ ።
ወኢይትዋሥኡ ፡ በኵሉ ።
ወስደው ፡ አልወሰድንም ፡ አይበሉ ።

፲ ፡ እላ ፡ ያሠንዩ ፡ በንጹሕ ፡ ሃይማኖቶሙ ።
በንጽሕና ፡ ኾነው ፡ በመታመን ። በመታመን ፡ ኾነው ፡ በንጽሕና ፡ ግብራቸውን ፡ ያከናውኑ ፡ እንጂ ።
ከመ ፡ ይንዓድዋ ፡ በኵለሄ ፡ ለትምህርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኃኒነ ። (ም ፡ ፩ ፡ ፫ ።
መድኃኒታችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስተማራት ፡ ወንጌልን ፡ ሕዝቡም ፡ አሕዛቡም ፡ ያከብሯት ፡ ዘንድ

፲፩ ፡ እስመ ፡ ተዐውቀት ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ። (ም ፡ ፫ ፡ ፬ ። ፩ ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፱ ።
ጸጋው ፡ ወንጌል ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ታውቃለች ፡ ተረድታለችና ።

፲፪ ፡ ወትሜህረነ ፡ ከመ ፡ ንትናከራ ፡ ለኃጢአት ።
ኃጢአትን ፡ እንለያት ፡ ዘንድ ፡ ታስተምረናለችና ።
ወለፍትወተ ፡ ዓለም ።
ፈቲውንም ፡ እንለያት ፡ ዘንድ ።
ወንሕየው ፡ በጽድቅ ፡ ወበንጽሕ ፡ ወበተፋቅሮ ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ። (ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፬ ። )
በዚህ ፡ ዓለም ፡ በፍቅር ፡ በንጽሕና ፡ በጽድቅ ፡ ጸንተን ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ ትሜህረነ ።

፲፫ ፡ እንዘ ፡ ንሴፎ ፡ አብዕዮ ። (፩ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፊል ፡ ፫ ፡ ፳ ። )
ብፅዓን ፡ መስጠቱን ፡ ተስፋ ፡ አድርገን ።
ወምጽአተ ስብሐቲሁ ፡ ለእምላክነ ፡ ዓቢይ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
በጌትነት ፡ መምጣቱን ፡ ተስፋ ፡ አድርገን ። አንድም ፡ አብዕዮ ፡ ምጽአተ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ይላል ፡) በጌትነት ፡
መጥቶ ፡ ብፅዓን ፡ መስጠቱን ፡ ተስፋ ፡ አድርገን ፡ ንሕየው ፡ በጽድቅ ።

፲፬ ፡ ዘመጠወ ፡ ርእሶ ፡ በእንቲአነ ፡ (ገላ ፡ ፩ ፡ ፬ ፡ ፩ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፮ ።)
ራሱን ፡ ስለኛ ፡ አሳልፎ ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ የሰጠ ።
ከመ ፡ ይቤዝወነ ፡ እምኃጢአት ።
ከኃጢአት ፡ ይለየን ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ከፍዳ ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ዘመጠወ ።
ወይንጽሕ ፡ ሎቱ ፡ ሕዝበ ፡ ሐዲሰ ።
ወገኖቹን ፡ ለሱ ፡ ማደሪያ ፡ ለመኾን ፡ የበቁ ፡ ሐዲስ ፡ ልጆች ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ።
ወይትቀነዩ ፡ በምግባረ ፡ ሠናይ ። (ኤፌ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡)
በምግባር ፡ በትሩፋት ፡ የሚፈካከሩ ።

፲፭ ፡ ከመዝ ፡ ንግር ፡ ወገሥጽ ።
እንዲህ ፡ ምከር ፡ አስተምር ።
ወተዛለፍ ። ዝለፍ ።
እንዘ ፡ ታቴሕት ፡ ርእሰከ ፡ ለኵሉ ።
ትሕትናን ፡ ይዘህ ።
ወአልቦ ፡ ዘያስሕተከ ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ፡ )
የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ ስሑት ፡ ነው ፡ የሚልህ ፡ ሰው ፡ አይኑር ፡ አንድም ፡ ስሑት ፡ የምትባልባትን ፡
ሥራ ፡ አትሥራ ።

፩ ፡ ተዘከሮሙ ፡ ለቀደምት ፡ ወለመኳንንት ።
ቀሳውስት ፡ ዲያቆናትን ፡ ምከራቸው ፡ አስተምራቸው ።
ከመ ፡ ይትኤዘዙ ፡ በኵሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫) ።
በበጎ ፡ ምግባር ፡ ኹሉ ፡ ጸንተው ፡ ይታዘዙ ፡ ዘንድ ፡ ዘከሮሙ ።
ወይኩኑ ፡ ጥቡዓነ ፡ በቱ ።
በዚያው ፡ ጸንተው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ዘከሮሙ ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፡ ወኢይትቆየሉ ።
    እንዳይበሳጩ ።
ወኢይትገአዙ ።
    እንዳይጣሉ ፡ እንዳይከራከሩ ።
አላ ፡ መሐርያነ ፡ ወየዋሃነ ፡ ይኩኑ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ። (ፊል ፡ ፬ ፡ ፭ ፡)
    ከሰው ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ መሀርያን ፡ ይኹኑ ፡ እንጂ ፡ አይትቆጥኡ ፤ የዋሃን ፡ ይኹኑ ፡ እንጂ ፡ አይትገአዙ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ንሕነሂ ፡ ትካት ፡ አብድነ ፡ ዘእንበለ ፡ አእምሮ ።
እኛም ፡ እኮ ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ባለማወቅ ፡ ስንፈን ፡ ነበር
ወክህድነ ። ክደን ፡ ነበር ።
ወስሕትነ ። ከሕግ ፡ ወጥተን ፡ ነበር ።
ወተቀነይነ ፡ ለፍትወት ።
    ለፈቲው ፡ ተገዝተን ፡ ነበር ።
ወለሐውዝ ፡ ዘዘዚአሁ ።
    ልዩ ፡ ልዩ ፡ ለሚኾን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ተገዝተን ፡ ነበር ።
ወተለዉነ ፡ እኩየ ።
    በክፉ ፡ ግብር ፡ ጸንተን ፡ ነበር ።
ወተቃንየ ።
    መቃናትን ፡ ይዘን ፡ ነበር ።
ወእሕሰምነ ፡ ወጸላዕነ ፡ ቢጸነ ፡ (፩፡ ቆር ፡ ፮ ፡ ፲፩ ። ኤፌ ፡ ፪፡ ፪፡ ፬፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ። )
    ወንድሞቻችንን ፡ እናሳዝን ፡ እንጠላ ፡ ነበር ።

፬ ፡ ወአመ ፡ አስተርአየ ፡ ምሕረቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ መድኃኒነ ። (ም ፡ ፪ ፡ ፲፩ ። )
    ቸር ፡ ሰው ፡ ወዳጅ ፡ የሚኾን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ቸርነቱ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ።

፭ ፡ አኮ ፡ በምግባረ ፡ ጽድቅነ (ኤፌ ፡ ፪ ፡ ፰ ፱ ።
    በሙያችን ፡ በጉልበታችን ፡ አይደለም ።
ዳዕሙ ፡ በምሕረቱ ።
    በቸርነቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቸርነቱ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ።
አድኀነነ ፡ በጥምቀት ፡ ዳግም ፡ ልደት ፡ (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፮ ። )
    ዳግም ፡ ልደት ፡ በሚባል ፡ ጥምቀት ፡ ዳግም ፡ ልደትን ፡ በሚያስከትል ፡ ጥምቀት ፡ ከዚህ ፡ ኹሉ ፡ አዳነን ።
ወተሐድሶ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ።
    በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመታደስ ፡ አዳነን ። እንድም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ተሐድሶን ፡ በሚያስከትል ፡ ጥምቀት ፡ አዳነን ።

፮ ፡ ዘሦጠ ፡ ላዕሌነ ፡ በብዕሉ ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኃኒነ ። (ኢዩ ፡ ፫፡፩ ፡ ሕዝ ፡ ፴፮ ፡ ፴፭ ።)
    ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለካሰልን ፡ በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ሀብቱን ፡ አብዝቶ ፡ ባሳደረው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፯ ፡ ከመ ፡ ንጽደቅ ፡ በጸጋሁ ። ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፩ ። )
    በቸርነቱ ፡ እንከብር ፡ ዘንድ ።
ወንረስ ፡ ተስፋ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ። (ሮሜ ፡ ፰ ፲፯ ።)
    የማታልፍ ፡ መንግሥት ፡ ስማይን ፡ እንወርስ ፡ ዘንድ ።

፰ ፡ እሙን ፡ ነገር ።
    ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ።
ወበእንተዝ ፡ እፈቅድ ፡ ታጽንዖሙ ።
    ስለዚህ ፡ ትመክራቸው ፡ ታስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ እወዳለሁ ። እንድም ፡ (አጽንዕከ) ፡ በሐዋርያነት ፡ ላጸናህ ፡ እወዳለሁ ።

ከመ ፡ የሐልዩ ፡ ተራድኦ ፡ በኵሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ እለ ፡ ተአመኑ ፡ በእግዚአብሔር ።
    በእግዚአብሔር ፡ ያመኑት ፡ ምእመናን ፡ በበጎ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ መረዳትን ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፡ እፈቅድ ፡ ታጽንዖሙ ።

www.ethiopianorthodox.org

ዝኬ ፡ ሠናይ ፡ ዘይበቍዖ ፡ ለሰብእ ። (ቍ. ፲፬ ።)
ለሰው ፡ የሚረባው ፡ የሚጠቅመው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ነዋ ።

፱ ፡ ነገረ ፡ ጋዕዝ ።
የጸብዕ ፡ የክርክርን ፡ ነገር ።

ወዕበድ ። የስንፍናን ፡ ነገር ።
ዘይፈጥሩ ። ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ የሚናገሩትን ።

ወመኃድምት ።
የተረትን ፡ ነገር ።

ወወከሕ ።
የዋዛ ፡ የፌዛዝን ፡ ነገር ፡ የሚናገሩትን ።

ተገሐሦሙ ።
(ተገሐሦሙ) ፡ ተለያቸው ።

እስመ ፡ ከንቱ ፡ ውእቱ ።
ከንቱ ፡ ነውና ።

ወኢይበቍዕ ። ፩ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፯ ።
አይረባም ፡ አይጠቅምምና ።

፲ ፡ ለመስተካህድ ፡ ብእሲ ፡ እምከመ ፡ ምዕረ ፡ ወካዕበ ፡ ገሠጽከ ፡ ወእበየ ፡ ኅድጎ ። (፪፡ዮሐ ፡ ፲ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፭ ።
ተከራካሪን ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ከረታኸው ፡ በኋላ ፡ አልመለስም ፡ ቢል ፡ ተወው ።

፲፩ ፡ ወእምሮ ፡ ከመ ፡ ዓላዊ ፡ ውእቱ ።
ኀብቶ ፡ ወጥ ፡ እንደኾነ ፡ እስታውቅበት ።

ዘከማሁ ፡ ያስሕት ፡ ወያጌጊ ።
እንደሱ ፡ ያለውን ፡ የሚያስት ፡ እንደኾነ ።

ወይረክብ ፡ ኵነኔ ። (፩፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፬ ፡ ፭ ። )
ፍዳውን ፡ እንዲቀበል ፡ አስታውቅበት ።

፲፪ ፡ ወእምከመ ፡ ፈነውኩዎ ፡ ለአርጢሞን ፡ ኀቤከ ።
አርጢሞንን ፡ ወዳንት ፡ በሰደድሁት ፡ ጊዜ ።

አው ፡ ጢኪቆስ ።
ጢኪቆስንም ፡ ቢኾን ፡ በሰደድሁት ፡ ጊዜ ።

ፍጡነ ፡ ነዓ ፡ ኀቤየ ፡ ሀገረ ፡ ናቆጵል ። (፪ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ።
እኔ ፡ ካለሁበት ፡ ዘንድ ፡ ናቆጵል ፡ ፈጥነህ ፡ ና ።

እስመ ፡ አጥባዕኩ ፡ እክርም ፡ ህየ ።
ከዚያ ፡ ልከርም ፡ ወድጃለሁና ።

፲፫ ፡ ለዜማስ ፡ ጸሐፊ ፡ ሀገር ፡ ወለአጵሎስ ፡ ጽሑቀ ፡ አከብሮሙ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፰፡ ፳፬፡ ፩፡ ቆሮ፡ ፩፡ ፲፪ ።)
ሀገር ፡ አሳዳሪ ፡ ዜማስንና ፡ አጵሎስን ፡ ተግተህ ፡ እርዳቸው ።

አይጸነሱ ፡ ምንተኒ ።
በምንም ፡ በምን ፡ እንዳይቸገሩ ።

፲፬ ፡ ወእሊአነሂ ፡ ይትመሀሩ ፡ ትምህርተ ፡ ሠናየ ፡ (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፳፰ ። )
(እሊአነ ፡ ) ምእመናን ፡ በጎውን ፡ ትምህርት ፡ ይማሩ ።

በዘይቀውሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስተ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ግብር ።
መምህራን ፡ በማስተማር ፡ ጸንተው ፡ በሚኖሩ ፡ ገንዘብ ።

ከመ ፡ አይንጥኡ ፡ (ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ፡ )
ምእመናን ፡ ፍሬ ፡ ትምህርትን ፡ እንዳያጡ ።

አንድም ፡ ወእሊአነሂ ፡ ይትመሀሩ ፡ ትምህርተ ፡ ሠናየ ።
መምህራን ፡ በጎውን ፡ ነገር ፡ ይማሩ ፡ (አለ ፡ ) ሠርተው ፡ ሥሩ ፡ ይበሏቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

በዘይቀውሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስተ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ግብር ።
ምእመናን ፡ በበጎው ፡ ግብር ፡ ጸንተው ፡ በሚኖሩ ፡ ገንዘብ ፡ ከመ ፡ ኢይኅጥኡ ።
ምእመናን ፡ ፍሬ ፡ ትሩፋትን ፡ እንዳያጡ ።

፲፭ ፡ አምኁከ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ምስሌየ ።
ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ኹሉ ፡ ቸር ፡ አሰሀን ፡ ይሉሃል ።
አምኅ ፡ ኵሎ ፡ ዘያፈቅረነ ፡ በሃይማኖት ።
በሃይማኖት ፡ የሚመስለንን ፡ ኹሉ ፡ ቸር ፡ እላችሁን ፡ በል ።
ጸጋሁ ፡ የሀሉ ፡ ምስለ ፡ ኵልከሙ ። (ገላ ፡ ፰ ፡ ፲ ።
እድሮባችሁ ፡ ይኑር ።

አሜን ፡ በውነት ።

ተፈጸመት ፡ መልእክት ፡ ኀበ ፡ ቲቶ ፡ ወተጽሕፈት ፡ በሀገረ ፡ ናቆጵል ፡ ወተፈነወት ፡ ምስለ ፡ አርጣማ ፡ ረድኡ ።
በናቆጵል ፡ የተጻፈች ፡ በአርጣማ ፡ እጅ ፡ ከጳውሎስ ፡ ለቲቶ ፡ የተላከች ፡ ከታብ ፡ ደረሰች ፡ ተፈጸመች ።

ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።
አነሣሥቶ ፡ ላስጀመረን ፡ አስጀምሮ ፡ ላስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

www.ethiopianorthodox.org